# ወደ ክርስቶስ የሚያድግ ጤናማ ሕይወት (ክፍል 1)

## I. በጤናማ ሕይወት ማደግ

- ማቴ 6፤22-23

ወደ ክርስቶስ የሚያድግና ጤናማ ________________________
የሆነን ሕይወት አማኝ መሻትና ________________________
መለማመድ አለበት ________________________

ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ ጤናማ ________________________
ያልሆነ እድገትን ከሚያስከትሉ ________________________
ነገሮች አማኝ ራሱን መጠበቅ ________________________
ይገባዋል ________________________

- ጤና መሆን ፡ - ደስታን ያጎናጽፋል
  - ተስፋን ያለመልማል
  - ስራን በአግባቡ መስራት ያስችላል

- ጤና አለመሆን ፡ - ደስታን ያሳጣል፣
  - ተስፋን ያጨልማል፣
  - ስቃይን ያበዛል
  - ስራን በአገባቡ መስራት ያዳግታል

- ጤና ለመሆን የሚከተሉት ነገሮች አስፈላጊ ናቸው

*i)* ለእድገት የሚረዱ ጠቃሚ ምግቦችን መመገብ
- ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚሆን ምግብ

*ii)* ጤናን ከሚመርዙ ነገሮች መጠበቅ

*iii)* ጤና ሲታወክ ቶሎ በመንፈስ መታከም

ጤናማ አማኝ የሚከተሉት ባሕሪያት አሉት ፦

1. *ኃጢያትን የሚጠላና ጽድቅን የሚለማመድ ሕይወት አለው*

- <u>ኃጢያት</u> - የእ/ርን ጽድቅ መተላለፍ፣ መውደቅ፣ መልካሙን ነገር መሳት (1ዮሐ 3፣4 ; ያዕ 4፣17 ዳን 9፣5)

- <u>የእ/ር ጽድቅ</u> - ትክክል፣ ቅዱስ፣ መልካም...የሆነ ነገር (ኃጢያተኛ የሆነውን ሰው ነጻ የሚያደርግ፣ በክርስቶስ በኩል የተሰጠ)

- ኃጢያት ሲኖር ከእ/ር ጋር መለያየት ይፈጠራል፣ሕብረታችንም ይበላሻል ብሎም ይቋረጣል (ኢሳ 59፣1-2)

- *ጤናማን ሕይወት ለመምራት ፦*
  - ዕለት ዕለት የሚገጥምን ፈተናን ማለፍ ( 1ቆሮ15፣31-34)

  - ራስን እየጎሸሙ ለእ/ር መገዛት *<u>ለምሳሌ</u>* ፦ ቅዱስ ያልሆነን ፍላጎትን፣ ምኞትን፣ ምርጫን፣ አካሄድን... (1ቆሮ 9፣26-27)

  - ሸክምንና ቶሎ የሚከበንን ኃጢያት ለማስወገድ መስዋዕትነት መክፈል (ዕብ12፣1-2)

2. *<u>እ/ርን የሚፈራና የሚወድድ ሕይወት</u>*

- እ/ርን መፍራት የሚመጣው ስለ እርሱ ያለን ግንዛቤ ባደገ ቁጥር ነው (ኢዮ 42፣5-6)
- ሰለ እርሱ የያለን ዕውቀት በጨመረ ቁጥር ቅዱስ ፍርሃት በውስጣ ችን እያደገ ይመጣል
  - ቅድስናውን፣ ክብሩን፣ ታላቅነቱን፣ ፈራጅነቱን፣ ዘላለማዊነቱን

- በዚህ መሰረት በንጹሕ ልብ የሚገለጽ አክብሮታችን እየጨመረና እርሱን እየወደድነው እንመጣለን
  - አኗኗራችን፣ አስተሳሰባችን፣ ተግባራችን፣ አነጋገራችን ወዘተ.. እ/ርን ማዕከል ያደረገና እርሱን የሚያከብር ይሆናል (ምሳ 1፣7) የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ...
- እ/ርን ከመፍራት ጋር እርሱን መውደድ የጤናማ አማኝ ምልክት ነው (ኢዮ 1፣1;5)
- የምንኖርባት ዓለም በጥፋት እየረከሰች ስትሄድ አማኝ ጽድቅን አብዝቶ በመኖር ዓለምን መኮነን አለበት *<u>ለምሳሌ-</u>* እንደ ኖኅ፣ሎጥ ዳንኤል ወዘተ (2ጴጥ 2፣7-8)

- በምድር ላይ ያሉ ሰዎች እንደ እ/ር ሊወድዱአቸው የሚችሉ ነገሮች አሉ *ለምሳሌ* - **ገንዘብን መውደድ** ( በገንዘብ መገልገል አለ ) 1ጢሞ 6፣10

  - **የሥልጣን (የክብር) ጥመኛ መሆን** ( እ/ር የሚሰጠው ሥልጣንና ክብር አለ ) አዶንያስ፦ 1ነገ 1
  - **ለሚያልፍ ለዚህ ዓለም ደስታ ራስን አሳልፎ መስጠት** (ከጌታ ብቻ የሚገኝ ደስታ አለ) ዕብ12፣16

- ጤናማ አማኝ በፍጹም ሁለንተናው እ/ርን ይወድዳል (ማር12፣29-30)

- እ/ርን መውደዳችን የሚታወቀው ባለን *ታዛዥነትና ታማኝነት* ነው (ዮሐ14፣23-24 ማቴ24፣45-51)

## *3. የእ/ርን ዘላለማዊ ፍቅር ለሌሎች የሚያካፍል ሕይወት*

- የምስራቹን ወንጌል ዘወትር መናገር (ኢሳ52፣7)
  - ለአንድም ይሁን ለብዙ ሰዎች
  - በአደባበይ ይሁን በጓዳ

- የመንግስታት ብርታት በታጠቁት መሣሪያና በያዙት ሠራዊት ብዛት ነው የወንጌል ብርታት ግን *በመልዕክቱ ኃያልነትና ባለው ሥልጣን* ነው
  - መልዕክቱ ማንንም የማንበርከክ ችሎታ አለው
  - መልዕክቱን ለማድረስ የማንንም በጎ ፈቃድ የሚጠይቅ አይደለም <u>ምሳሌ</u> የሐዋርያት አገልግሎት

- የወንጌል መልዕክት ለሰዎች የሚነገራቸው ስለ እ/ር መንግስት መረጃ እንዲኖራቸው ሳይሆን በመልዕክቱ ተግባራዊ ለውጥ እንዲኖራቸው ነው (ሉቃ 4፣19)
  - በመንፈስ ለደኸዩ፣ በሥጋም ሆነ በአእምሮ ድሆች ለሆኑ የሕይወት ብልጽግናን ማጎናጸፍ
  - የኃጢያት ምርኮኛ ሆነው የታሰሩትን ነጻ ማውጣት
  - ልባቸው በተለየየ ነገር የተሰበረውን መጠገን
  - መንፈሳዊና ሥጋዊ ፈውስን በነጻ ለሰዎች ማደል